## 1.መግቢያ

ብዙ የአገራቸው ሁኔታ የሚያንገበግባቸው ኢትዮጵያዊያን በሲያትልና በዙሪያዋ ይገኛሉ።እነዚህ ዜጎች በአገራቸው ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የፖለትካ ውዥንብር እንዴት ይመለከቱታል ?ስለአገራቸው ሁኔታስ መረጃ የሚያገኙት ከየት ነው ? በማንኛው የፖለቲካ ድርጅትስ ላይ ነው እምነት ያላቸው ? አሁን በስልጣን ላይ ያለውንስ ገዢ መደብ እንዴት ያዩታለ ?የሚሉ ሃሳቦች መልስ ለማግኘት ሲባል አንዲት ትንሽየ መጠይቅ ተዘጋጅታ ተበተነች።

የቀረቡት አስራ ስድስት ጥያቄዎች ሲሆኑ እያንዳንዱ ሰው ከተሰጡት አማራጮች መካከል በመሰለው ሃሳብ ላይ ምልክት በማድርግ ስሜቱን እንዲገልጽ ተደርጓል።በዚህች አነስተኛ ስርቬይ ላይ የተካፈሉት ከሁለቱም ጾታ የተወጣጡ በእድሜ ገደባቸው ለአቅመ አዳም የደረሱ አማርኛ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ኢትዮጵያዊያን ናቸው።

ጥያቄው ከተዘጋጀ በኋላ ኢትዮጵያዊያን በብዛት በሚገኙበት አካባቢ በመሄድና በማስራጨት እንዲሁም በሃበሻ ሱቅ ውስጥ በማስቀመጥና እዚያ የሚመጡ እትዮጵያዊያን እንዲሞሉት በማድረግ አስተያየታቸውን ለማሰባሰብ ጥረት ተደርጓል።

አራት መቶ መጠይቆች ተበትነው ሶስት መቶው ተሰብስቧል።ይህም ከታሰበው በላይ በመሆኑ የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ አመለካከት ይወክላል የሚል እምነት አሳድሯል።

ጥናቱን ይበልጥ የተዋጣለት ለማድረግ የጊዜ እጥረት መኖሩ እንደ ጥናቱ ችግር የተያዘ ቢሆንም ይህች አነስተኛ ሰርቬይ ለፖለቲካ ድርጅቶች ህውሃትን ጨምሮ እንደ አንድ ግብአት ልታገለግል እንደምትችል ተስፋ እናደርጋለን።

## 2.የጥናቱ እጥረቶች

የአንዳንድ ኢትዮጵያዊያን መስመር የለቀቀ ጥርጣሬ። አለ አይደለም ሁሉንም የሚጠረጥር "cynical" የሆነ አእምሮ ያለው ሰው። ማነው ይህን የሚጠይቀው ? ለምንድ ነው የሚጠይቀው ? ምን ሊያረግበት ነው ?የሚሉ ጥያቄዎችን የሚጠይቁ ።ለጥያቄያቸው በቂ መልስ ቢሰጣቸውም ለማመን ፈቃደኝነት በማጣትና ሌሎችም እንዳይሞሉት ያከላከሉ ሰዎች መኖራቸው።

አልፎ አልፎ እርስ በርሱ የሚጣረዝ መልስ የሚሰጡ ሰዎች በመኖራቸው ምክንያት እንዲህ አይነት ወረቀቶች ለአተረጓጎም ስለማያመቹ ወጥተው ተጥለዋል።

ጥናቱን ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ለመስራት በቂ ጊዜ ባለመኖሩ በተገኘ ትርፍ ግዜ ብቻ የተዘጋጀ በመሆኑ መካተት የነበረባቸው ጠቃሚ ነገሮች በሙሉ አልተካተቱም የሚል እምነት መኖሩ።

## 3.የጥናቱ ብሳ ጎኖች

መጠይቆቹ አጭርና ግልጽ በመሆናቸው የሚሞላውን ሰው ጊዜ መቆጠብ መቻላቸው።

መጠይቁን የሞሉት ኢትዮጵያዊያን "Randomly" የተገኙ መሆናቸው።

ጥናቱን ያካሄዱት በገዛ ፈቃዳቸው የተነሳሱ በሲያትል አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሲሆኑ እስከ አሁን በተደረገው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ምንም ተሳትፎ ያልነበራቸው ናቸው።

## <u>ክፍል አንድ</u>

### ህወሃት/ኢህአዴግን ማን ብሎ ይጠሩታል ?

አብዛኛው ሰው በአካባቢው ስለሚያየው ነገር የራሱን ግንዘቤ በመውሰድና ያንኑ ግንዛቤ እውቀት አድርጎ ይዞ የመኖር ልምድ አለው።ግንዛቤው ትክክልም ይሁን ስህተት አንዴ ተገንዝቦታልና ለብዙ ጊዜ አብሮት ይኖራል።ይህን ለረዥም ገዜ አብሮ የኖረን አስተሳሰብ የሚያስቀይር አንዳች አይነት ምክንያት ካገኘ ግን ግንዛቤው የማይቀየርበት ሁኔት አለ ብለን አናምንም።

ከህወሃት/ኢህአዴግ ተግባራት በመነሳት ህዝቡ ለዚህ "መንግስት" ነኝ ለሚል አካል ያለው ግንዛቤ የሚያስገርም ነው።በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያለፍ መንግሥታት በሙሉ አምባገነን ሲባሉ እናውቃለን እንጂ አምባገነንም ዴሞክራትም ያልሆነ ***ማፊያ*** የሚል ስም ሲሰጠው ወያኔ የመጀመሪያው ነው።ለምን ቢሉ በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል።ከብሄራዊ ባንክ ውስጥ ለክፍ ቀን የተቀመጠ ወርቅ ወጥቶ ተወስዶ በአሮጌ ባሌስትራ ከመተካቱ አንስተን ለነብስ አድን የተሰጠን እርዳታ ሽጦ በግል ባንክ አካውንት ማስቀመጥን በልዩ ልዩ ዜዴ የአገሪቷ ዜጎች ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከሚወዷት እናት አገራቸው አገዲስደዱና እንዲገደሉ መደረጋቸውን ችጋር በተለየ ሁኔታ የነገሰበትንና የወያኔ አባላትን ሃብት ብዛት መጥቀስ ይቻላል።

ታዲያ ኢትዮጵያዊያኑ ይህን ድርጅት እንዴት ያዩታል ?ለመሆኑ ህወሃት/ኢህአዴግን እንደ ዴሞክራሲ ሃዋሪያ የሚያየው አለን ?ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ስንል የሚከተለውን ጥያቄ አቅርበን 300 ሰዎች መልስ የሰጡ ሲሆን ውጤቱን እንደሚከተለው አቅርበናል።

| በእርስዎ አስተያየት ህወሃት/ኢህአዴግ ምንድ ነው ? | ዴሞክራት | አምባገነን | ሁለቱንም ያልሆነ ማፊያ ነው |
|---|---|---|---|
| | 0<br>0% | 133<br>44% | 167<br>56% |

ህወሃት/ኢህአዴግ በእብሪት ተወጥሮ በስህተት ላይ ስህተት ከመፈጸም ውጭ ለምን እንዲህ አይነት አጸያፊ ስም ተሰጠኝ ብሎ ራሱን የሚጠይቅና እርምት ለማድረግ ራሱን የሚያዘጋጅ ድርጅት ነው ብለን አናምንም።የሆነ ሆኖ በዚህ ስሙና እብሪቱ እስከ መቼ ይቀጥል ይሆን?

በተጨማሪም ህወሃት/ኢህአዴግን በተለያዩ ስሞች የሚገልጹት ኢትዮጵያዊያን አሉ።የዚህ ድርጅት መገለጫዎች ብዙ ናቸው እኛም ደጉንም ክፉንም ቀላቅለን መላሾች በሚመስላቸው ቃል/ሃረግ ላይ ምልክት እንዲያደርጉበት የጠየቅናቸው ሲሆን ውጤቱም እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፤

| አባክዎትን ህወሃት/ኢህአዴግን ይገልጻሉ ብለው በሚያምኑት ቃል/ሃረግ ላይ ምልክት በማድረግ ያመልክቱ | ለኢትዮጵያ በጎ ራእይ ያለው | ፍጹም የወርበላዎች ጥርቅም | ፍጽም ዘረኛ | ዲሞክራት | ጸረ ኢትዮጵያ | ለኢትዮጵያ አንድነት ጠንክሮ የሚሰራ | ውሸታም | ለህግ የበላይነት ጠንክሮ የሚሰራ | ኢትዮጵያን ለማፍረስ ጠንክሮ የሚሰራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 0<br>0% | 194<br>65% | 205<br>68% | 0<br>0% | 194<br>65% | 0<br>0% | 198<br>66% | 0<br>0% | 201<br>67% |

ለኢትዮጵያ በጎ ራእይ ያለው፡ዴሞክራት፡ለኢትዮጵያ አንድነት ጠንክሮ የሚሰራ፤ለህግ የበላይነት የሚታገል የሚል ምርጫ የተሰጠ ቢሆንም አንድም ሰው በነዚህ ምርጫዎች ላይ ምልክት አላደረገም።ህወሃት/ኢህአዴግ ይህን የኢትዮጵያዊያንን አስተያየት ሲያይ ምን ሊል እንደሚችል ባናውቅም ይህ ከኢትዮጵያዊያን የተገኘው አስተያየት የሚያመለክተው ግን ይህ ገዢ መደብ ዝም ብሎ የራሱን ጩኅት ብቻ ሰምቶ በዚያው ተደስቶ ተኩራርቶና አብጦ የሚኖር አካል መሆኑን ነው።

ወያኔ ይህን ውጤት የማያምነው ከሆነና እኔ እንዲህ አይደለውም ካለ ይህችኑ ጥያቄ በገለልተኛ አካል በማስጠየቅ እውነቱን ማገኘት ግድ ይሆንበታል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## ነገረ መለስ ዜናዊ

**መለስ** ዜናዊ ነገረ ብዙ ነው።የሱ ነገር መቸስ ገርሞን ገርሞን አብቅተናል።ይህ ሰው ከነገሰ እነሆ ሰላሳ አመት ሆነው አይደል ? የዚህ ሰው ደጋፊዎች መለስ ዜናዊን ጠንካራ ጀግና እያሉ ሲያወድሱት ሌሎች ደግሞ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት በሌሉበት ይህ ሰው ጠንካራ ሊባል አይችልም ብለው ይከራከራሉ።መለስ ዜናዊ ጠንካራ ከተባለም የጥንካሬው ምንጭ የሚሆነው በዚያች አገር ውስጥ የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጡ ተቋማት አለመኖራቸው ብቻ ነው ይላሉ።እንዲያውም መለስ ዜናዊ በጣም ፈሪና ደካማ ስለሆነ የሚቀናቀነውን ተከራክሮ ከማሸነፍ ይልቅ በውሸት ከሶ ማሳደድ፤ ማጥፋት፤ማሰርና መገደል ቀዳሚ ተግባሩ ነው ብለው ያክላሉ።

የመለስ ዜናዊ ዘመነ ንግስና የሚታወቀው በሙስና፤በዝርፊያ፤በግዲያ እና በሰብአዊ መብት ጥሰት ነው እንጂ በሌላ በጎ ነገር አይደለም።ይህ ሰው የሚጠላው የሰው ልጅ የማያደርገውን ክፍ ነገር በማድርጉ ነው እንጂ አንድ ቅን አስተሳሰብ ያለው ዲክታተር የሚያደርገውን በማድረጉ አይደለም።

የቀድሞ የመለስ ዜናዊ ወዳጆች እንደነገሩን ከሆነ የሃውዜንን ህዝብ በረቀቀ ብልሃትና ጭካኔ በደርግ ጄቶች እንዲደበደቡ አድርጎ ሲያበቃ በሰለጠኑ ፎቶ አንሺዎችና ቪዲዮ ቀራጮች አስቀርጾ የፖለቲካ ጠቀሜታ አግኝቶበታል።ምንም እንኳን የረከሰ ተግባር ቢሆንም ለእርሱ ግን ትልቅ ድል ነበር የሆነለት።ወደ መሃል አገር ሰተት ብሎ ከገባ በኋላም በጋምቤላ በአንዲት ጀንበር 400 ሰዎች እንዲገደሉ አድርጓል፡በምርጫ ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ 197 ሰዎች በጥይት ተመትተው እንዲሞቱ ቀጥታ ትእዛዝ ሰጥቷል፤የአገሪቷን ድንበር አፍርሶ በደምና አጥንት የቆየውን መሬት አሳልፎ ለባእዳን ሰጥቷል እንዚህና ሌሎች ወንጀሎች ሲደማመሩ በአገር ክዳትና በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሶና ጥፋተኛ ተብሎ እንደ ሳዳም ሁሴን አንዲት ትንሽየ ገመድ ባንገቱ ገብታ

የማይንጠለጠልበት ምንም ምክናያት የለም።መለስ ይህን ከማንም በላይ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ እንደ ሂትለር የደረሰበት ሳይታወቅ ራሱን ማጥፋት ይመርጣል እንጂ ሲሳለቅ ባደገበት ፍትህ ፊት ለመቆም በምንም ሁኔታ አይፈቅደም።እስከዚያ ድረስ ግን ያሻውን እያደገ እቀርጣለሁ ያለውን እየቀረጠ የሚገድለውን እየገደለ የኖራል። እኛም እርሱ ሲፈቅድልን ብቻ በሰላም መኖር እንችላለን።

ከዚህ በመነሳት መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ በፍጹም በሰላማዊ መንገድ ስልጣን እንደማይለቁ የሚስማሙ ኢትዮጵያዊያን አሉ።ለመሆኑ ስንት የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን በዚህ ሃሳብ ይስማሙ ይሆን ?እስኪ አብረን እንይ፤

| አቶ መለስና ጓደኞቹ በፍጹም በሰላማዊ መንገድ ስልጣን የመልቀቅ ፍላጎት የላቸውም የሚሉ በርካቶች ናቸው እርስዎ በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ ? | እስማማለሁ | አልስማማም |
|---|---|---|
| | 277<br>92% | 23<br>8% |

ለዚህ ጥያቄ 300 ሰዎች መልስ የሰጡ ሲሆን ይህንኑ ጥያቄ ለዘብ አድርገን እንደገና ጠይቀነው ያገኘነው ውጤት እንደሚከተለው ነው።

| መለስ ዜናዊ በድምጽ ብልጫ ተበልጠ በሰላማዊ መንገድ ስልጣን የሚለቅ ይመስሎታል ? | አይመስለኝም | አዎን ይመስለኛል |
|---|---|---|
| | 292<br>97% | 8<br>3% |

መለስ ዜናዊ በሰላማዊ መንገድ ስልጣን ለመልቀቅ ፈቃደኝነት በማጣቱ ምክንያት ኢትዮጵያዊያኑ ልዩ ልዩ የሙብትሄ ሃሳቦችን ሲሰነዝሩ ይደመጣሉ።እኛ እንደምናየው የሚጠቀሙት የሙብትሄ ሃሳቦች ሶስት ናቸው።ከ እነዚህ መካከል የትኛው መንገድ በኢትዮጵያዊያኑ ዘንድ ተመራጭ እንደሆነ ለማወቅ የሚከተለውን ጥያቄ አቅርበናል፤

| መለስ ዜናዊ በፍጹም በሰላማዊ መንገድ ስልጣን አይለቅም በሚለው ሃሳብ የሚስማሙ ከሆነ ምን መደረግ አለበት ይላሉ ? | ሰላማዊ ትግል ብቻ ማድረግ | የትጥቅ ትግል ብቻ ማድረግ | ሁለገብ ትግል ማድረግ |
|---|---|---|---|
| | 53<br>20% | 53<br>20% | 160<br>60% |

ለዚህ ጥያቄ 266 ሰዎች መልስ የሰጡ ሲሆን ሰላማዊ ትግል የሚሉና የትጥቅ ትግል የሚሉ ቁጥራቸው እኩል ነው።እዚህ ላይ የላቀ ጥናት የሚያስፈልገው ሃሳብ “መለስ ዜናዊ በሰላማዊ ትግል ስልጣን አይለቅም እናም ሰላማዊ ትግል ብቻ ማድረግ” የሚለው ነው።እንዴት አድርጎ ነው ይህን ተቃርኖ ያለበት ሃሳብ ማስታረቅ የሚቻለው? እንዴትስ ሁኖ ነው በሰላማዊ ትግል ብቻ በሰላማዊ መንገድ ስልጣን የማይለቅን አንድን የማፊያ ስብስብስብ መሪ ነው ተብሎ የሚታመንን ሰው ከስልጣን ማስለቀቅ የሚቻለው ?ሰላማዊ ትግል የሚሉ ይህን በደንብ አድርገው ማስረዳትና ለውጥ ፈላጊውን ህዝብ ማሳመን ይኖርባቸዋል።

ከሰንጠርዡ እንደምናየው የአብዛኛው ሰው ምርጫ ሁለገብ ትግል ማድረግ ነው።የዚህ ትግል ስልት ባለቤት የሆነው ግንቦት7 እንቅስቃሴ ስለሆነ ይህን ጉዳይ ጥሩ አድርጎ በማስረዳት በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ ይጠበቅበታል።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በአገር ውስጥ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ያለውን ሁኔታ አበረታች ነው ብሎ አያምንም።ከዚህ ጋር በተያያዘ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ከሰጡ 289 ሰዎች መካከል 1%ቱ ብቻ አበረታች ነው ሲሉ 33%ቱ ደግሞ ጠባብም ቢሆን መንገድ እንዳለ የሚሰማቸው ናቸው።ቀሪዎቹ 66% ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለማድርግ ምንም አመቺ ሁኔታ የለም ብለው የሚያምኑ ሁነው ተገኝተዋል።

| ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለማድረግ ያለው ሁኔታ | አበረታች ነው | ጠባብም ቢሆንም መንገድ አለ | ምንም አመቺ ሁኔታ የለም |
|---|---|---|---|
| | 4<br>1% | 95<br>33% | 190<br>66% |

## ክፍል ሶስት

### እምነት የሚጣልበት የፖለትካ ድርጅት የትኛው ነው ?

በአንድ አገር ውስጥ ፖለቲካ መሪ ነኝ ለሚል ድርጅት የሚያስፈልገው አንድ ትልቅ ነገር ቢኖር የዜጎችን እምነት ማግኘት መቻሉ ነው።በዚያች አገር ውስጥ ብልጽግናና ሰላም አመጣልሃለሁ የሚል የፖለቲካ ድርጅት አስቀድሞ እቀምለታለሁ የሚለለትን ህዝብ እምነት ማግኘትና ያንን ህዝብ በመሳሪያ ሃይል ሳይሆን በፈቃደኝነት የማስከተል አቅም ሊኖረው ይገባል።ከዚህ አንጻር ህወሃት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያዊያንን እምነት አገኝቷል ለማለት የሚያስደፍር አንዳችም ምልክት አላየንም።እንዲያውም በተቃራኒው ኢትዮጵያዊያኑ ይህን ድርጅት የሚመለከቱት አገርን ለማፍረስ የቆመ የወሮበላዎች ጥርቅምና ውሽታም እንደሆነ ነው።

ኢትዮጵያዊያኑ እምነት የሚጥሉበት የፖለቲካ ድርጅት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ በማሰብ የሚከተለውን ጥያቄ አቅርበንላቸው ነበር። “በእርስዎ እምነት ቀጥሎ ከተጠቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል እምነት የሚጥሉበት ድርጅት የትኛው ነው ?” 1.መድረክ 2.ኦነግ 3.የአርበኞች ግንባር 4.ግንቦት 7።ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል ኦነግ የቆየ የትግል ታሪክ ያለው ቢሆንም ያገኘው ድምጽ .8% ብቻ ነው።መድረክ 20% አዎንታዊ መልስ ሲያገኝ የአርበኞች ግንባር ደግሞ በ30% በሚሆኑ መላሾች ዘንድ እምነት የሚጣልበት ድርጅት ሁኗል።ቀሪው 50% ኢትዮጵያዊ ደግሞ በግንቦት ሰባት ላይ እምነቱን ያሳደረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።የአርበኞች ግንባር የትጥቅ ትግል ቀደም ብሎ የጀመረ ድርጅት ሲሆን ግንቦት 7 ንቅናቄ ደግሞ ሁለገብ ትግል ማድርግ የትግሉ ስልት እንደሆነ አሳውቋል።ኦነግ እምነት የሚጥልበት ኢትዮጵያዊ ቁጥር አነስተኛ መሆን የሚያሳስብ ጉዳይ ሳይሆን አይቀርምና ድርጅቱ የኢትዮጵያዊያኑን እምነት ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለበት ቆም ብሎ ማሰብ ይጠበቅበታል።በሌላ በኩል የአርበኞች ግንባርና ግንቦት ሰባት ንቅናቄ በተቻለ ፍጥነት ውህደት ቢፈጥሩ በድምሩ 80% የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያንን ድጋፍ ማግኘት እንደሚችሉ ከዚህች ሰርቬይ ለመረዳት ይቻላል።

| በ እርስዎ እምነት ቀጥሎ ከተጠቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ እምነት የሚጥሉበት ድርጅት የትኛው ነው ? | መድረክ | ኦነግ | የአርበኞች ግንባር | ግንቦት7 |
|---|---|---|---|---|
| | 53<br>20% | 2<br>0.8% | 76<br>30% | 129<br>50% |

በዚህ ክፍለ ውስጥ ህወሃት/ኢህአድግ እንደ አንድ አማራጭ መካተት ነበረበት ብለው አስተያየታቸውን የለገሱን እህቶች ነበሩ።በእርግጥ መካተት ነበረበት። ይህም የሰርቬዩ አንዱ ደካማ ጎን ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነገር ቢሆንም ይህ ድርጅት በዚህ ክፍል አለመካተቱ ግን ከላይ የተገኘውን ውጤት ሊያዛባው የሚችል ነገር አይሆንም።ምክንያቱም ህዝቡ ህወሃት/ኢህአዴግን የሚያየው እንደ አምባገነንና ማፊያ ቡድን ስለሆነ ምን አይነት እምነት ሊጥልበት ይችላል?

## ክፍል አራት

## የግል ሚና አለኝን

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ህወሃት/ኢህአዴግ እያዘገመ ያለበት መንገድ አደገኛ እንደሆነ ይስማማል።ይህን ጉልበተኛ የሚመስልን ሃይል ታግሎ መጣል የሚቻል ስለማይመስለው ተስፋ ቆርጦ በየቤቱ ዝም ብሎ የተቀመጠ ኢትዮጵያዊ ብዙ ነው። ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው ትግለ ውስጥ በግሉ ሚና ይኖረኛል ብሎ ከማሰብ ይልቅ ሌሎች ለውጡን ቢያመጡለት ደስተኛ የሚሆን እትዮጵያዊ በርካታ ሳይሆን አይቀርም።ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚከተለውን ጥያቄ አቅርበን የመላሾችን ስሜት ለመረዳት ሞክረናል።

| ህወሃት/ኢህአዴግ ለኢትዮጵያችን በጎ ነገር አያደርግም ብለው የሚያምኑ ከሆነ ህወሃት/ኢህ አዴግን ለመቀየር በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሚና ይኖረኛል ብለው ያምናሉ ? | አዎን አምናለሁ | ሚና አለኝ ብየ አልምንም |
|---|---|---|
| | 239 | 42 |
| | 85% | 15% |

ለዚህ ጥያቄ 281 ኢትዮጵያዊያን መልስ ሰጥተዋል።

ይህ ህውሃት/ኢህአዴግን ከሚኒልክ ቤተ-መንግስት አባሮ መልካም አስተዳደርን ለማምጣት ትግል ለሚያደርጉ ድርጅቶች መልካም ዜና እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን።በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማምጣት በተለያዩ የፖቲካ ድርጅቶች አማካኝነት የሚደረገውን ትግል መደገፍ ይፈልጉ እንደሆን ተጠይቀው 94%ቱ አዎን እንፈልጋለን ሲሉ 6%ቱ ደግሞ አንፈልግም ብለዋል።እነዚህ ፍላጎቱ ያላቸው የትኛውን የፖለቲካ ድርጅት ይደግፉ እንደሆን ለማወቅ ባቀረብነው ጥያቄ መሰረት 22%ቱ መድረክን 23%ቱ የአርበኞች ግንባርን 2%ቱ ኦነግን 3%ቱ ሌላ በሚለው አማራጭ ላይ ምልክት ያደረጉ ሲሆን ቀሪዎቹ 52% ደግሞ የግንቦት ሰባት እንቅስቃሴን ለመደገፉ ፍላጎት ያላቸው ሁነው ተገኝተዋል።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ ውስጥ መልካም አስተዳደርን ላማምጣት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አማካኝነት የሚደረገውን ትግል መደገፍ ይፈልጋሉ ? | አዎን እፈልጋለሁ<br>274=94% | | አልፈልግም<br>19=6% | | |
| መደገፍ የሚፈልጉ ከሆነ የትኛው የፖለትካ ድርጅት ቀልቦን ይስበዋል | ግንቦት 7 | መድረክ | አርበኞች ግንባር | ኦነግ | ሌላ |
| | 156=52% | 67=22% | 68=23% | 7=2% | 3=1% |

ለመጀመሪያው ጥያቄ 293 ለሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ 233 ኢትዮጵያዊያን መልስ ሰጥተዋል።

## ክፍል አምስት

### ነገረ ሃይሉ ሻውል

ሰሞኑን ኢትዮጵያዊያኑን ጉድ ጉድ ያሰኘው የመወያያ ርእስ የአቶ ሀይሉ ሻውል ነገር ነው።ይህኙ ሰው የሼህ አላሙዲን ንብርት በሆነው በሸራትን አዲስ ወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ በታሰረች በ304ኛው ቀን ከህውሃት/ኢህአዴግ ጋር ውል ፈጽመው ከድርጅቱ መሪ ከሆኑት ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር መጨባበጣቸውን ያየ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ልዩ ልዩ አስተያየቶችን ሲሰጥ ሰንብቷል።ትላንት ባገር ክደት ተከሰው የእድሜ ልክ እስራት ሲጠየቅባቸው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአንድ ድምጽ ከጎናቸው ጸንቶ ቁሞ ነበር።ምን ባደረጉ ነው አገር ከዱ የሚባለው ብሎ ያላዘነ አልነበረም።አሁን ደግሞ ነገሩ ሁሉ ተገልብጦ ከትላንት ከሳሾቻቸውና ፈራጆቻቸው ጋር ሁነው ድግስ ተደግሶላቸውና ነጋሪት ተጎስሞላቸው እነሆ በቤተ-መንግስቱ ውስጥ በአንድ ገበታ ዙሪያ ስናያቸው የሆደ ሰፊው ወያኔ ነገር እጅግ ገረመን።

ትላንት እንዴት ከሃዲ ይባሉብናል ብሎ በየጎዳናው ድምጹን ከፍ አድርጎ ስለ ሃይሉ ሻውል ሲሟገት የከረመው የኢትዮጵያ ልጅ ሁሉ አሁን ተደረገ የተባለውን ስምምነት እንደ ክህደት እንደሚቆጥረው ስለተሰማንና በዚህ ጉዳይ ላይም ህዝቡ ምን እንደሚል ማወቅ ስለፈለግን የሚከተለውን ጥያቄ ለመጠየቅ ተገደድን።ጥያቄው እንደሚከተለው ቀርቧል፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰሞኑን አቶ ሃይሉ ሻውል ከህወሃት/ኢህአዴግ ጋር ያደረጉትን ውል እንዴት ያዩታል ? | እንደ አንድ ትልቅ ድል | እንድ ክህደት | አይመለከተኝም |
| | 8 | 224 | 49 |
| | 3% | 80% | 17% |

ባጠቃላይ ለዚህ ጥያቄ 281 እትዮጵያዊያን መልስ ሰጥተዋል።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ጆሮአችን ድንቅ ነገር ሰማ አይናችንም መልካም ነገር አየ ብለው ደስ ያላቸው የህወሃት ፍጡሮች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ኢትዮጵያዊያን እንደ አንድ ትልቅ ድል በመቁጠር ደስ ብሏቸዋል።ሆኖም ግን ከ281 መላሾች መካከል 8(3%) ብቻ በመሆናቸው የሃይሉ ሻውልን ገጽታ ሊያሻሽለው የሚችል ነገር አይመስለንም።

49(17%) መላሾች ከብስጭት ሊሆን ይችላል ይህ ጉዳይ አይመለከተንም ብለዋል።ከእነዚህ መካከል የሁለቱን አስተያየት አናቀርብና እናበቃለን እንዲህም ይነበባል "ስነ ምግባር የጎደለው ብቻ ነው ስነ ምግባር ስነ ምግባር እያለ የሚለፈልፈው የሆኖ ሆኖ ይህ ጉዳይ አይመለከተኝም" ሌላው ደግሞ "ይህን ጉዳይ የማየው እንደ ቆምጬምባው የጉሪጥ ነው"ብሏል።

በሲያትል የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አቶ ሃይሉ ሻውል ከቅንጅት መሪዎች ጋር ሁነው በታሰሩ ጊዜ የክረምቱ በርዶ ሳይበግራቸው በየአደባባዩ ፎቶአቸውን በትልቁ አሰርተውና ተሸክመው እየተሰለፉ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አቶ ሀይሉ ይፈቱ ዘንድ በየአደባባዩ ሲጮሁ እንደነበር እናስታውሳለን።አቶ ሀይሉ ግን በውጭ ያለውን ደጋፊያቸውን አናንቀው ሲናገሩ ሰምተን ተገርመን ተገርመን አብቅተናል።የተከበሩት አቶ ሃይሉም የሚተማመኑትን ተማምነው ደጋፊዎቻቸውንም አፍንጫችሁን ላሱ ብለው ወደ ሚኒልክ ቤተ-መንግስት አቅንተዋል። ለዚህም እፎይ ተገላገልን ከማለት ውጭ ሌላ የምንለው የለንም።

## ማጠቃለያ

**ህወሃት/ኢህአዴግ** ከዚህ ሰርቬይ የሚማረው ቁም ነገር ይኖራል ብለን ተስፋ የምናደርገው ነገር የለም።የመማር ፍላጎት የሌው ብቻ ሳይሆን ተምሮም የሚገባው ስላልሆነ ለዚህ መንፈሳዊ ጥንካሬ ለሌው ድርጅት የምንለው ምንም ነገር የለም።

ህወሃት/ኢህአዴግን ከህግ በታች በማድረግ በኢትዮጵያችን ፍትህ እኩልነት ዴሞክራሲና ነጻነት ሰፍኖ ለማየት የምትፈልጉ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ የህወሃት ጥንካሬው የኢናንተ መከፋፍልና ትናንሽ ተቃዋሚ መሆን ብቻ መሆኑን አውቃችሁ ለላቀው ለአገር ጥቅም ስትሉ በሚቻለው ሁሉ አንዳች አይነት ግንባር መፍጠር ይጠበቅባችኋል።ይህም የአጠቃላይ ኢትዮጵያዊ ፍላጎት ነው።

ወያኔ መንፈሰ ሙት ቢሆንም በገዘፈ አካሉ ደካማ ይመስለችኋልን ? ለመግደል ለማሰር ህግ ለመጣስና ማንኛውንም ኢሰብአዊ ድርጊት ለመፈጸም ሰውሰንም የማያፍር እግዚአብሄርንም የማይፈራ ኀይል አይደለምን?! እንዚህን ድርጊቶች ለመፈጸም ጉልበት የሚያገኘው ደግሞ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች አንድ መሆን ካለመቻላቸው የተነሳ አይደለምን?! ስለሆነም በተለይ በሰላማዊ ትግል ተሰፋ የቀረጣችሁ ኀይሎች ጊዜ ሳታጠፍ አንድ ግንባር መፍጠር ያልቻላችሁት ለምንድ ነው ? ድር ካላበረ አንበሳን ማሰር እንደማይችል አታውቁምን ? አዎን ! አፍንጫ ሲመታ አይን ያልቅስ። ማልቀስ ያለበትም ጊዜ አሁን ነው።ግንቦት 7፤ኦነግ፤አርበኞች ግንባር፡ኦብነግ እና ሌሎችም አንዳች አይነት ግንባር የማትፈጥሩት ለምንድ ነው ? ሌላውን ችግሮቻችንን ለመወያየትና የጋራ መብትሄ ለመፈልግ ነጻነት የከለከልን ወያኔ አይደልምን ?እርሱን ክህግ በታች ለማድረግና ነጻ አገር ለመመስረት እንዳትተባበሩ የሚያግዳችሁ ከቶ ምን ይኖር ይሆን?

ቸር እንሰንብት

ሰው ለሰውና ጓደኞቹ

ከሲያትል